# ግድያና ዉድመት መወገዝ አለበት፤
# እንዳይደጋገሙም በህብረት መቆም አለብን

ከዶ/ር በቀለ ገሠሠ

## 1ኛ/ እየተካሄደ ያለዉ ጭፍጨፋ፤ ዝርፊያና ዉድመት እጅግ አሳዛኝነት፤

መከራችን እየባሰበት ሄደ። ባንድ በኩል ቀሳፊዉ ኮሮና ቫይረስ/ተዋስ፤ በሌላዉ በኩል ግድያ፤ ንብረት ማዉደምና ማፈናቀል። ዛሬ የሚካሄደዉ ነገር በኢትዮጵያችን ምድር መሆኑን ማመን እያቃተኝ ነዉ። አገሪቷ የደጋግ ህዝብ ምድር ነበረች። በርግጥ ቀይ ሽብር ተካሂዶ በተለይ ንፁሐን ወጣቶችን እንዳወደመ ታሪክ ሲያስታዉሰዉ ይኖራል። የዛሬዉ ደግሞ ብሶበታል። ዜጎች ምንም በማያዉቁትና ባላጠፉት ምክንያት በተለይ ዘርና ኃይማኖት እየተቆጠረ አሰቃቂ ጥቃት በመድረስ ላይ ይገኛል። በዕድሜ የገፉ አዛዉንት፤ እርጉዞችና እናቶች፤ ወዘተ፤ ጭካኔ በተሞላ አረመኔያዊ እርምጃዎች ክፉኛ እየተጠቁ ይገኛሉ። የነዚያ ንፁሐን ዜጎች ደም በከንቱ ፈሰሰ፤ ንብረታቸዉ በከንቱ ወደመ። የተረፉት በገዛ አገራቸዉ መኖር አቅቷቸዉ በየአብያተ ክርስቲያናትና በደጋግ ሰዎች ቤት ተጠልለዉ በከባድ ሲቃይ ላይ ይገኛሉ። ስለወደፊቱም ምንም ዋስትና የላቸዉም። ለምን? ለምን? ለምን?

የነዚህ ንፁሐን ዜጎች ደም ወደእግዚአብሄር/አላህ እየጮኼ ነዉ። ጭፍጨፋዉን የተመለከቱ የቤተሰብ አባላት፤ በተለይ ሕፃናት ምን ዓይነት የሥነ ልቦና ቀዉስ ሊደርስባቸዉ እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም።

እግዚአብሔር ግድያንና ዉድመትን ይቃወማል፤ አትግደል ይላል። እንደዚሁም፤ አላህ የንፁሐን ዜጎችን ግድያና እንግልት ይቃወማል። ስብዕናችንም አይፈቅድም። ዛሬ ያለንበት የሰዉ ስልጣኔ ደረጃም አይፈቅድም። ማንኛዉም ሕግ አይፈቅድም። በዐለምም ሕዝብ ፊት ማፈሪያዎች ሆነናል።

## 2ኛ/ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

በዉዷ አገራችን ዉስጥ እየተካሄደ ያለዉ ጭፍጨፋ፤ ዝርፊያና ዉድመት ሁላችንንም እኩል ማሳሰብ ይኖርበታል።

- ♣ ሁላችንም እኩል ማዘን አለብን፤
- ♣ ሁላችንም እኩል ማፈር አለብን፤
- ♣ ሁላችንም እኩል ነገሮችን ለማስተካከል መጣር አለብን። መተባበር አለብን።

በዚህ መንገድ ለሥልጣን የሚቋምጡ ርካሽ የፖሊቲካ ቡድኖች ማፈር አለባቸዉ። ወጣቱም ቢሆን በነዚህ ዓይነት ሰዎች በጭፍን መነዳት የለባቸዉም። የእነዚያ የሚገደሉ ንፁሐን እናቶች ነፍስ ልክ እንደገዛ እናቶቻቸዉ ነፍስ መቁጠር ይኖርበታል፤ የስብፀና መሰረታዊ መስፈርት ነዉና።

የተቃዋሚ ፖሊቲካ ድርጅቶች በይፋ ወጥተዉ ወንጀሎቹን መኮነን ይጠበቅባቸዋል። ጥፋቶቹም እንዳይደጋገሙ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። መጠፋፋት ለማንም እንደማይበጅ ማወቅ ይኖርባቸዋል። የነሩዋንዳን ታሪክ ባይረሱ ይሻላል።

መንግሥት ደግሞ ሀ) ነፍሰ ገዳዮቹን በሙሉ ለፍርድ ማቅረብ፤ ለ) በግፍ የታሰሩትን ነፁሐን ዜጎች ለይቶ ቶሎ መፍታት፤ ሐ) ጉዳት የደረሰባቸዉን ዜጎች መታደግና መልሶ ማቋቋም ይጠበቅበታል። ያ መከረኛዉም ሕገ መንግሥት የሚሻሻልበትን መንገድ ማመቻቸት እጅግ አስፈላጊ ነዉ ብዬ አምናለሁ። ለአንድነታችንም፤ ለድንበሮቻችንም፤ ለግድባችንም፤ ወዘተ ዋስትና ከሚያስጠብቁ ሁኔታዎች መሃል ጠንካራ ሕገ መንግሥት ዋናዉን ቦታ ይይዛል።

ብሄርና ኃይማኖት ሳይለዩ ባንድ ላይ ሆነዉ ለዲሞክራሲ ግንባታ ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ የቀድሞ ንፁሐን ዜጎች ደም እንዳይፋረደን ብንጠነቀቅ ይሻላል።

እምነትና ራዕይ ያለዉ ህዝብ ከዘመን ወደዘመን በዕድገት ጎዳና ይራመዳል። የኛ ጉዞ ግን ሁልጊዜ ወደኋላ መሆኑ እጅጉን ያሳዝነኛል። ሰላም ቢኖረን አገራችን ሃብታም ነበረች። ስለዚህ አምላካችን ጥሩ ልቦና ይስጠን። እባካችሁን ወደ ቀድሞዉ ሕልዉናችን እንመለስ። ህብረታችንና አንድነታችንን እናጠንክር። ተያይዞ ከመጥፋት ተያይዞ መነሳት ይሻላል።

ቸሩ ፈጣሪያችን ይጠብቀን።